# ኢትዮጵያችን

## ለ2017 የ"ፈረንጆቹ" አዲስ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ

**ጋዜጣዊ መግለጫ** ታህሳስ 23 ቀን 2009 ዓ.ም. (January 01, 2017)

**ለ ፦ YaTewlid**

በቅድሚያ የከበረ ሰላምታችንን እያቀረብን፤ እንኳን ለ2017 የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት አደረሳችሁ። አዲሱ ዓመትም በሀገራችን ኢትዮጵያ የሕዝባዊ ትግሉ ድል የሚቀዳጅበትና የዴሞክራሲያ ጮራ ሚፈነጥቅበት ያደርግልን ዘንድ እንመኛለን።

***ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖች!***

መስከረም 08 ቀን 2009 ዓ.ም. (September 18, 2016) እራሱን ለሕዝብ ይፋ ያደረገው "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (አሀ! አሕ! ኢሕን)" ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከጀመረ እነሆ አራት ወራት ሆኖታል። ሀገራችን ኢትዮጵያ ህልውናዋንና አንድነቷን ጠብቃ በእድገትና የልማት ጎዳና ትጓዝ ዘንድ ዓላማው አድርጎ የተነሳው "አሀ! አሕ! ኢሕን" የሀገሪቷ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ትኩረቱን በሀገር ቤትና የትግሉ ተሸካሚ ምሰሶ የሆኑትን ወጣቱ ትውልድና ሴቶች እህቶቻችንን በከፍተኛ ደረጃ በማሳተፍ "ኢትዮጵያችን ንቅናቄ" ሕዝባዊ ትግሉን ከዳር ለማድረስና የሁሉም ልጆቿ የሆነች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚከፈለውን ግዳጅና መስዋዕትነት ለመክፈል ዘብ መቆማችንን ለመላው ሕዝባችን በመግለጽ በድጋሚ ቃል እንገባለን።

***"አሀ! አሕ! ኢሕን" ዋና ዋና ዓላማዎች ፦***

- ዘረኛውን የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ለመጣልና ሕዝባዊ መሠረት ያለው አገዛዝ በሀገራችን ለማስፈን ሕዝቡን በማስተባበር ለሕዝባዊ ንቅናቄ ማነሳሳት
- የኢትዮጵያንና የሕዝቧን አንድነት ባስጠበቀ መልኩ ፀረ-ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ትግሉን ከሌሎች ሕዝባዊ ኃይሎች ጋር በጋራ ለመታገል
- በዘር የተከፋፈለ ፖለቲካ ቦታውን ለኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ይለቅ ዘንድ መሥራት
- የኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነትና የሕዝቧ ዴሞክራሲያዊ አንድነት በሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎት ላይ በተመሠረተ ሕገ መንግሥት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ መሥራት ናቸው።

እነዚህን ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ "አሀ! አሕ! ኢሕን" የራሱን

ፕሮግራምና (http://www.ethiopiachen.org/images/1_Hagere_1_Hizb_Programme.pdf)
ማንፌስቶ (http://www.ethiopiachen.org/images/pdf/1_Hager_1_Hizb_Manfesto_Public.pdf) ቀርጾ በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆን፤
የንቅናቄው ድረ ገጽ www.ethiopiachen.org. www.ethiopiachen.com መሆኑንና
እንዲሁም ወቅትን ጠብቆ የሚወጣ የንቅናቄው ልሳን "ኢትዮጵያችን" የሚል መሆኑን በድጋሚ ልናሳውቅ እንወዳለን።

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ይዞ በተነሳው ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማ መሠረት ከተለያዩ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶችም ሆነ የሃይማኖት ተቋማት ጋር በሀገራችን የጋራ ጉዳይ ላይ አብሮ ለመስራትና ለመምከር ያለንን ቀና አመለካከት ለማሳወቅ እንወዳለን። በተጨማሪም ለሁሉም የመገናኛ ተቋሞች (ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ . . .)፣ ፓል ቶክ ክፍሎች፣ ድረ ገጽ አካላት፣ መወያያ መድረኮች ወዘተ. ለሀገራችንና ለሕዝባችን የምታደርጉትን ጥረት እያደነቅን በአዲሱ የፈረንጆቹ ዓመት 2017 ተባብሮና ተደጋግፎ ለመጓዝ ቀና ልቦና ይሰጠን ዘንድ ድምጻችንን እናሰማለን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ethiopiachen2009@gmail.com

ታህሳስ 23 ቀን 2009 ዓ.ም. (January 01, 2017)

**ግልባጭ፦**

በሀገር ቤትና በውጭው ዓለም ለሚንቀሳቀሱ

- የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች በሙሉ
- የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተቋማት
- ለመገናኛ ብዙሃን (ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት ወዘተ)
- ፓል ቶክ ክፍሎች
- ድረ ገጽ ባለቤቶች
- መወያያ መድረኮች